የስብሰባ ጥሪ

ለሕብረት ባንክ አ.ማ. ባለአክሲዮኖች በሙሉ

የባለአክስዮኖች 29ኛ መደበኛ እና 15ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤዎች የስብሰባ ጥሪ

በኢፌዲሪ ንግድ ሕግ አንቀጽ 366 (1) ፣ 367 (1 እና 2)፣ አንቀጽ 370 እንዲሁም በአክሲዮን ማኅበሩ መመሥረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 14 መሠረት የሕብረት ባንክ አ.ማ. የባለአክሲዮኖች 29ኛ ዓመታዊ መደበኛ እና 15ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤዎች **ሐሙስ፣ ጥቅምት 12 ቀን 2019 ዓ.ም. ከጠዋቱ 2:00 ሰዓት ጀምሮ በሸራተን አዲስ ሆቴል** ስለሚካሄድ የባንኩ ባለአክሲዮኖች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተጠቀሰው ቀን፣ ሰዓትና ቦታ በስብሰባው ላይ እንዲገኙ የባንኩ የዲሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

1. ማህበሩን የሚመለከቱ ዋና ዋና መረጃዎች

1.1.	የአክሲዮን ማኅበሩ ዋና መሥሪያ ቤት አድራሻ	አዲስ አበባ፣ ልደታ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 07፣ የቤት ቁጥር አዲስ
1.2.	የባንኩ ድረ-ገጽ	http://www.hibretbank.com.et
1.3.	የአክሲዮን ማህበሩ የምዝገባ ቁጥር	LLB/006/98
1.4.	የአክስዮን ማኅበሩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ ብር (ካፒታል)	11,665,497,000.00
1.5.	የአክስዮን ማኅበሩ የተከፈለ ዋና ገንዘብ ብር	8,174,336,406.58

2. የ29ኛ ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች

2.1	የስብሰባውን አጀንዳ ማጽደቅ፣
2.2	የአክሲዮን ዝውውር ማሳወቅ፣
2.3	እ.ኤ.አ የ2025/2026 በጀት ዓመት የዲሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት ላይ ተወያይቶ ማጽደቅ፣
2.4	እ.ኤ.አ የ2025/2026 በጀት ዓመት የውጭ ኦዲተሩ ሪፖርት ላይ ተወያይቶ ማጽደቅ፣
2.5	እ.ኤ.አ የ2025/2026 በጀት ዓመት የባንኩን ዓመታዊ የትርፍ ክፍፍል መወሰን፣
2.6	እ.ኤ.አ የ2025/2026 የዲሬክተሮች ቦርድ አባላትን ዓመታዊ የአገልግሎት ክፍያና እ.ኤ.አ የ2026/27 ወርኃዊ ክፍያ መወሰን፣
2.7	የስብሰባውን ቃለጉባኤ ማጽደቅ፤

3. የ15ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች

3.1.	የስብሰባውን አጀንዳ ማጽደቅ፣
3.2.	ተፈርመው ባልተከፈሉ አክሲዮኖች አከፋፈል ላይ ተወያይቶ መወሰን
3.3.	የስብሰባውን ቃለጉባኤ ማጽደቅ፤

4. ማሳሰቢያ

4.1 በጉባኤው ላይ መገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች ተወካዮቻችሁ፣ ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ የተሰጠ የውክልና ሰነድ ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ በመያዝ ወይም በንግድ ሕጉ አንቀጽ 377 መሠረት፣ ጉባኤው ከመካሄዱ ከሦስት ቀናት በፊት ባንኩ ያዘጋጀውን የውክልና መስጫ ሰነድ፣ ሰንጋተራ በሚገኘው በባንኩ ዋና መ/ቤት ሕብር ታወር 24ኛ ፎቅ የባንኩ አክሲዮን ክፍል ድረስ ቀርቦ በመፈረም ሌላ ባለአክሲዮን ለመወከል የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን፤ ሆኖም አንድ ባለአክስዮን በማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በማንኛውም ችሎታ መወከል የሚችለው አንድ ሰው ብቻ ስለመሆኑ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

4.2 የአክስዮን ማኅበሩ ባለአክሲዮኖች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በጉባኤው ላይ ለመሳተፍ ሲመጡ፣ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸውን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፈቃድ ዋናውንና ኮፒ በመያዝ በጉባኤው ላይ መሳተፍ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሆኑ የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው የማኅበሩ ባለአክሲዮኖች ትውልደ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ቀኑ ያላለፈበት መታወቂያ (ቢጫ ካርድ) ይዘው መቅረብ እንዳለባቸው በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡

4.3 ውክልና ይዘው የሚገኙ ባለአክሲዮኖች በውክልና ሊይዙ የሚችሉት የውክልና መጠን፣ (የራሳቸውን አክስዮን ጨምሮ) ከባንኩ የተፈረመ ካፒታል ከአሥር በመቶ ሊበልጥ አይችልም፡፡

4.4 በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር SBB/91/2024 አንቀጽ 20 (3) መሠረት፣የባንኩ የቦርድ አባላትና ሠራተኞች በየትኛውም የባለአክሲዮኖች ስብሰባ ላይ ማንኛውንም ባለአክሲዮን ወክለው መገኘት አይችሉም፡፡

ሕብረት ባንክ አ.ማ
የዲሬክተሮች ቦርድ